በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ነሐሴ 13 ቀን 2014 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት 12ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔዎች

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 12ኛ መደበኛ ስብሰባ በሁለት ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ።

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የግብርና ምርት አምራችና አስመራች ግንኙነትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ላይ ነው፡፡ ከአምራቾች ጋር በሚደረግ ውል የግብርና ምርቶችን በስፋት ማምረት እንዲቻል፣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የሚያስችሉ የእውቀት፣ ክህሎትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ብሎም የገበያ ትስስር የሚፈጠርበት የአምራች እና የአስመራች ግንኙነት በተሟላ የሕግ ማዕቀፍ የሚመራበት ሥርዓት በመዘርጋት የአምራቾችን ተጠቃሚነት በላቀ ደረጃ ለማረጋገጥ የሚያስችል ህግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ረቂቅ አዋጁ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

2. ምክር ቤቱ በመቀጠል የተወያየው የዕጽዋት ዘር ረቂቅ አዋጅ ላይ ሲሆን በሥራ ላይ ያለው የዕጽዋት ዘር አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 782/2005) አገራችን በግብርናው ዘርፍ እያስመዘገበች ከምትገኘው ዘርፈ ብዙ የግብርና እመርታዎች ጋር ሲታይ ክፍተቶች ያሉት በመሆኑ፣ አሁን ግብርናው ከደረሠበት ደረጃ አኳያ የዕፅዋት ዘር አቅርቦትን በጥራት፣ በዓይነትና በመጠን በዘላቂነት ማምረት እንዲቻል፤ የአገሪቱ የዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪን ለማዘመን፣ ቴክኖሎጂና ኢንቨስትመንት በመሳብ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማሳደግ፣ በአገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ ላሉ አግሮ ኢንደስትሪዎች የግብዓት አቅርቦት ለማሳደግ፣ መጠባበቂያ የእጽዋት ዘር አያያዝ ሥርዓት ለመዘርጋት እና ተያያዥ አስቻይ ሁኔታዎችን ለማሟላት ይቻል ዘንድ የአዋጁ መሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ከተወያየ በኋላ ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

//